EAAD-NILE

Ethiopian-Americans ADHOC for Democracy

**P.O. Box 5243, Springfield, VA, 22150 E-mail: ethioabay2010@hotmail.com Telephone: (571) 269-5677**

ነሐሴ 5 ቀን 2010

# የምስጋና መልዕክት ከሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴ

ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ከአገር ጥቅምና ደህንነት በላይ የተሻለ ነገር የለም በማለት ከተለያዩ የአሜሪካ ስቴቶችና ከካናዳ ይህን የመሰለ ድንቅ የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ እዚህ በመገኘታችሁ የሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴው እጅግን ደስ ያላችሁ/እጅጏን ደስ አለን ይላል::

ጠቅለል ባለመልኩ ዛሬ እዚህ ያለነው ህዝባችን፣ መንግስታችንና ኤምባሲያችን በመደገፍ ነው::

አንኳር አንኳር ነገሮችን ለመጥቀስ ያህል:-

1. ከኢኮኖሚ አውታሮች አንዱ የሆነውን የአባይ ወንዝ ኢትዮጵያ የመጠቀም መብትዋን እንደግፋለን:: ይኸን ለማረጋገጥ ሲባል እኛ በያለንበት አካባቢ ሁሉ የሀገራችን አምባሳደሮች በመሆን ከማንኛውም አቅጣጫ የሚመጣን ተፅዕኖ ለመመከት ከህዝባችንና ከመንግስታችን ጋር ነን በማለት አረጋግጠናል::

2. ህዝባችን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ያጠናቀቀውን የግንቦት ወር አራተኛ ብሔራዊ ምርጫ ወሳኙ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው በማለት ደግፈናል:: በምርጫው ላይ ለተወዳደሩ ተቃዋሚዎችም አድናቆታችንን እንገልፃለን:: በስመ ሂዩማን ራይትስ ዎች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሌለ ነገር በማንሳት በሀገራችን ላይ ጣልቃ ለመግባት የሚሞክሩትን እንቃወማለን::

3. በቅርቡ በኡጋንዳ ዋና ከተማ በወገኖቻችን ላይ የተፈፀመውን የሽብርተኝነት ተግባር እንቃወማለን:: ከህዝባችን ጎን ተሰልፈን ድርጊቱን እንዋጋዋለን::

4. በገዛ አገራችን ላይ ወሳጅ፣ እህትና ወንድም አልባ አድርገውን ሲያበቁ በአሁኑ ወቅት በምዕራቡ አለም ተሸሽገው የአገራችን እድገት ወደኋሊት ለመጎተት የሚሯሯጡትንና በስመ ተቃዋሚ የአገራችን መልካም ስምና እድገት ጥላሸት የሚቀቡትን በመቃወም፣ የኢትጵያ ህዝብ በቃኝ ብሎ እንዳላቸው ሁሉ እኛም በቃን ብለን ያካሄድነው ሰልፍ ነው:: ሰላማዊና ገንቢ ተቃዋሚዎች መኖራቸው ለወደፊት እድገታችን መልካም ነው እንላለን::

5. የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት እያካሄዱት ያሉትን የልማት አቅጣጫና ተከታታይ እድገት ድህነትና ድንቁርናን ከአገራችን ለማጥፋት የሚደረግ ጥረት በመሆኑ በሙሉ ልብ እንደግፋለን::

EAAD-NILE

Ethiopian-Americans ADHOC for Democracy

**P.O. Box 5243, Springfield, VA, 22150 E-mail: ethioabay2010@hotmail.com Telephone: (571) 269-5677**

**ለማጠቃለል፤**

1. እዚህ ስልፍ ላይ ለመገኘት ጊዜያችሁንና ገንዘባችሁን ሰውታችሁ ለመጣችሁ ሁሉ ሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴው የላቀ ምስጋና ያቀርባል:: የአገር ፍቅር ጥማትና ስሜት ኖሯችሁ በተለያየ ምክንያት እዚህ ልትገኙ ላልቻላችሁና በስልክ፣ በኢሜይል፣ በቲዊተር እና በፌስቡክ ላበረታታችሁን እናመሰግናለን::

2. ይኸን ሰልፍ እውን ለማድረግ ጊዜያችሁን፣ ገንዘባችሁን፣ ጉልበታችሁንና እውቀታችሁን ላበረከታችሁ ሁሉ ሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴው ታላቅ ምስጋና ያቀርባል::

3. ለሀገር ፍቅር ሬዲዮ፣ ለአንድ ኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ ለሰላም ሬዲዮ እና በአትላንታ ለኢትዮጵያውያን ሬዲዮ ድምፅ ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን::

4. በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አሊያንስ ላደረገልን ትብብር ታላቅ ምስጋና እናቀርባለን::

5. በሰሜን አሜሪካ የትግራይ ማህበር ላደረገልን ያላሰለሰ ጥረትና ትብብር እናመሰግናለን::

6. ለአይጋ ፎረም፣ ኡትና እና ኢትዮጵያ ፈርስት ድህረ ገጾች ታላቅ ምስጋና እናቀርባለን::

7. ከኢትዮ ሲቪሊቲ ለተደረገልን ትብብር እናመሰግናለን::

8. በኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ለተደረገልን ትብብር እናመሰግናለን::

**እናመሰግናለን**

**ሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴ**